**አማረ ለምን አሁን የግድያ (የማስፈራሪያ) ሙከራ ተደረገበት**

**ከቅዱስ**

kidusl@yahoo.com

የአቶ አማረን የግድያ ሙከራ እና ማን ሊያደርገው ይችላል የሚለውን ከመጠየቅ በፊት ስለ አቶ አማረ ታሪክ ማወቁ ለአጠቃላይ ግንዛቤ ይረዳል ብዬ አምናለሁ:: ከዚህም በተጨማሪ አደጋው ከመድረሱ በፊት የነበሩት ማስጠንቀቂያዎች እና ማስጠንቀቂያዎቹ ከየት ሲመጡ እንደነበሩ ማወቁም ለግራ እና ቀኝ ይጠቅማል::

የሪፖርተር ጋዜጣ ባለቤት እና ዋና አዘጋጅ አማረ አረጋዊ ኢህአዴግን ቀድሞ በመተው የመጀመሪያው ከፍተኛ ባለስልጣን እንደሆነ ይነገርለታል::የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ስራ አስኪያጅ በነበረበት ወቅት የኢቴቪ የፕሮግራም ለውጥ የነበረበት መሆኑን ብዙዎቹ የሚስማሙበት ሲሆን የ«120»ን ፕሮግራም እና ሌሎችን በማስጀመር አማረ አረጋዊ ይታወቃል:: በወቅቱ በኢህአዴጎች የስልጣን ሹም ሽር ተካሂዶበት ከነበረው ስልጣን ዝቅ ብሎ እንዲሰራ ሲደረግ እናም ከነበሩት ቱባ ባለስልጣኖች ጋር ግጭት ውስጥ ሲገባ የመንግስት ስራ ትቶ እንደወጣ ይታወቃል:: ሪፖርተር በ1987 ዓ. ም. ጳጉሜ ላይ ሲመሰረት ሙሉ ህትመቱ በሜጋ ማተሚያ ቤት የነበረ ሲሆን በ«120» ፕሮግራም አዘጋጅነት የሚታወቀው ሰለሞን ገ/እግዚአብሔር እንዲሁም «ባለጉዳይ» በተባለው ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ላይ የሚተውነው እና ከሚሌኒየም አዘጋጅ ኮሚቴ አንዱ የሆነው አበበ ባልቻ በሚዲያና እና ኮሚኒኬሽን ሴንተር (MCC) ስር አብረውት የነበሩ ግለሰቦች ናቸው:: አበበ ባልቻ በ (MCC) ከአማረ አረጋዊ ጋር እኩል ሼር እንደነበረው የሚታወቅ ሲሆን ከጊዜ በኃላ ግን አማረ በብቸኝነት የድርጅቱ ባለቤት እንደሆነ ይታወቃል::

ጋዜጣው በመጀመሪያዎቹ አመታቶች በቀላሉ የማይገኙ መረጃዎች ሰጪነቱ በተጨማሪ «ደላላው እና ዳንዮት» የመሰሉ ጥሩ መጣጥፎች ነበሩ:: የ«ደላላው» አዘጋጅ ከበደ ደበሌ ሮቢ የጋዜጣው ኤዲተር የነበረ ሲሆን በቃላት ጥንካሬው እና በቋንቋው ውበት የታወቀ ነው:: የ«ዳንዮት» አምድ አዘጋጅ አብዶ (የደርግ ጊዜው የሬዲዮ ቃለ-መጠይቅ ማብራሪያ ሰጪ ጓድ አብዶ) በተለየ አጻጻፍ እና ህግ ነክ በሆኑ ጉዳዮች የታወቀ ጸሀፊ ነው:: «ዳንዮት» አምድ የቀረ ሲሆን «ደላላው» ከበደ ደበሌ ከሪፖርተር መልቀቅ ጋር አብሮ ውበቱን ያጣ አምድ ነው::

ሪፖርተር በህዝብ ዘንድ ይበልጥ መነበብ የጀመረው የቀድሞው ም/ጠ/ሚ ታምራት ላይኔ በ«ስኳር» ሰበብ ሲታሰር የውስጥ አዋቂነት ሚናውን በመጫወት አማረ በታምራት ላይኔ ግላዊ ህይወት ዙሪያ ተከታታይ ዜና (ጽሁፍ) ሲያወጣ ነው:: ቀጥሎም በንግድ ባንክ ዙሪያ ያሉ ሙስናዎችን በተከታታይ በማውጣት እንዲሁም ከባንክ ብድር እንዴት እንደሚገኝ እናም የባንክ ባለስልጣኖች ምን ያህል በሙስና የተዘፈቁ እንደሆኑ ያስነብብ ነበር:: በቴሌ እና በኢትዮጵያ አየር መንገድ ያሉትን የሙስና እና የአስተዳደር ችግሮችን በተከታታይ ሲያወጣ በወቅቱ በጉዳዩ የተነካኩ ባለስልጣኖች ለህይወቱ አስጊ ስለሆኑበት (በማስፈራራት) ለ2 ጊዜያት ያህል አሜሪካን አገር ለተወሰነ ጊዜ እንዲቆይ ተገዶ ነበር::

ቀጥሎም በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት እንዲሁ ተከታታይ እና መረጃ ሰጪ የሆኑ ጽሁፎችን ጋዜጣው በተቋቋመ በአመቱ በተመሰረተው «ሪፖርተር» መጽሄት በማውጣት ከፍተኛ ተነባቢነትን በተለይ በምሁሩ እና በወጣቱ ዘንድ ለማግኘት ችሏል:: የህወሀት (ወያኔ) መከፋፈል ሲፈጠር ሪፖርተር በተለይ ለነስዬ ቡድን እንደ ልሳን እስከማገልገል

ደርሶ ነበር፡፡ በሪፖርተር መጽሄት «የቤተ-መንግስት ቡድኑን» የሚያጋልጥ ተከታታይ ጽሁፍ ጥለው በወጡት አመራሮች ያወጣ ነበር፡፡

የ«ኔሽን» ጋዜጣ ሲመሰረት በርከት ያሉ የሪፖርተር አንጋፋ ጋዜጠኞች ሪፖርተርን በመልቀቅ በወቅቱ ወፈር ያለ ክፍያ የሰጣቸውን «ኔሽን» ተቀላቅለው ነበር፡፡ «ሪፖርተር »ም የበሳል ጋዜጠኞች ችግር የነበረበት ወቅት ነበር፡፡ «ኔሽን» በተመሰረተበት ሰሞን በከተማው ተወዳጅነትን እያተረፈ የነበረ ቢሆንም ብዙም በህትመት ሳይቆይ ለመክሰም በቅቷል፡፡ «ሪፖርተር»ን ለቀው የነበሩት ጋዜጠኞች ተመልሰው ሲመጡ አማረ «ቤታችሁ ነው መጀመሪያም ያስወጣችሁ አልበረም» በማለት ተቀብሏቸዋል፡፡ አዲሱ የፕሬስ ህግ ረቂቅ በወጣበት ጊዜ አማረ ክፉኛ ኢህአዴግን ይተች ነበር፡፡ በተለይ በአንድ ስበሰባ ላይ ከበረከት ስምኦን ጋር ዱላ ቀረሽ ክርክር በማድረግ ይታወቃል፡፡

በምርጫ 97 ሪፖርተር ጋዜጣ እና መጽኄት ሁለት የተለያየ እንድምታ ነበራቸው፡፡ የጋዜጣው አዘጋጅ አማረ አረጋዊ (የቀድሞው ኢህአዴግ) እና የመጽሄቱ አዘጋጅ (ስሙን አሁን የረሳሁት) የቅንጅት አባል እና ከስራው የአንድ ወር ፈቃድ ወስዶ በሰሜን ሸዋ ለቅንጅት ሲቀሰቅስ የነበረ ነው፡፡ መጽሄቱ ለቅንጅት የሚያደላ ጽኁፍ በምርጫው ወቅት የሚስተናገድበት ሲሆን ጋዜጣው ደግሞም የኢህአዴግን ነጯ ምርጫ የሚያወድስ ነበር፡፡ በተለይ ምርጫው ሊካሄድ ቀናት ሲቀሩት ለህትመት የበቃው «ሪፖርተር» መጽሄት የቅንጅት እና የኢህአዴግን የመጨረሻ የድጋፍ ሰልፍ በሚያነጻጽር መልኩ ያወጣው ምስል እና ጠ/ሚ/ር መለስ የቅንጅት አመራሮችን ሲገላምጡአቸው የሚያሳየው ምስላዊ ቅንብር እንዲሁም መጽሄቱ በውስጡ የያዘው መልእክት (ከርእሰ አንቀጽ እና ወቸጉድ አምድ ጀምሮ) የጋዜጣውና የመጽሄቱን የአቋም ልዩነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነበር፡፡ በወቅቱ በአማረ እና በቅንጅት ደጋፊ የሪፖርተር ጋዜጠኞች መካከል በሪፖርተር ቢሮ ውስጥ ሞቅ ያለ ክርክር እና ውይይት ይካሄድ ነበር፡፡ ከምርጫው ውጤት በኋላ በኢህአዴግና በቅንጅት መካከል በነበረው ግጭት አማረ በግልጽ የኢህአዴግን አቋም የሚደግፍ ተከታታይ ጽሁፎች አውጥቷል፡፡ ከአሰቃቂው የአግአዚው አልሞ ተኳሾች ጭፍጨፋ በኃላ ነገሮች ይበልጥ እየተካረሩ መጥተው ነበር፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ የ«ሪፖርተር» ጋዜጣ የሟች ቤተሰቦችን በመርካቶ አካባቢ በመጠየቅ ስለ አሰቃቂው ጭፍጨፋ ሰፋ ያለ ዜናዊ ትንታኔ ያቀርብ ነበር፡፡ ቅንጅት የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን በመሰብሰብ «ፓርላማ እንግባ ወይስ አንግባ» የሚል ውይይት በሚያደርግበት ወቅት አማረ አረጋዊ በአንዱ ስብሰባ በመጋበዝ ተገኝቶ ፓርላማ ለምን መግባት እንዳለባቸው ለሰብሳቢዎቹ የቅንጅት አመራሮች ማብራሪያ ሰጥቶ ነበር፡፡ በተከታታይ በርእሰ አንቀጹ የ«ፓርላማ ግቡ» ውትወታውን አላቋረጠም ነበር፡፡ ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር የነበራቸውም ግንኙነት መቀዝቀዝ የጀመረው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ አማረ በወቅቱ የዲያስፖራውን ፖለቲካ ክፉኛ ይተች የነበረ ሲሆን በአንድ ወቅት «ውሃ ውስጥ እየኖረ የማይረጥብ አሳ» በሚል ርእሰ-አንቀጽ የዲያስፖራውን ፖለቲከኞች ክፉኛ ወርፏል፡፡ በወቅቱ የአማረ አክራሪነት እና ኢህአዴጋዊ ወገንተኝነት የተሰማቸው ጋዜጠኞች በመሰብሰብ የያዘው ወገንተኛዊ አቋም ትክክል እንዳልሆነ ሊያስረዱት ሞክረዋል፡፡ አማረ «መርካቶ በጥብጦ ቤተ-መንግስት መግባት የለም፡፡ እንደዛ ከታሰበ እኛ በገባንበት መንገድ ትገባላችሁ» እስከማለት ደርሶ ነበር፡፡ የወቅቱ የአማረ ሁኔታ ከቅንጅት ጋር እልህ የመጋባት ይመስል ነበር፡፡የቅንጅት መሪዎች ከታሰሩ በኃላ አማረ ፊቱን ወደ ኢህአዴግ በማዞር ኢህአዴግ «ሲነገረው የማይሰማ» ድርጅት እንደሆነ እና በህዝብ ተቀባይነት ለመግኘት ተደጋጋሚ እድሎች የሚያመልጡት ፓርቲ እንደሆነ ያትት ነበር፡፡

«ክቡር ሚኒስትር» እና «ተስፍሽ እና ገብርሽ (ካርቱን)» እንዲሁም ርእሰ አንቀጹ ራሱ አማረ የሚያዘጋጃቸው ሲሆኑ በተለይ «ክቡር ሚኒስትር» የኢህአዴግ ባለስልጣኖችን ክፉኛ የሚተች አምድ ነው፡፡

ትናንሽ መንግስታት ፧ ሁለት ኢህአዴጎች ፧ የአላሙዲ ኢንቨስትመንት ሁኔታ ፧ መንግስት፧ ከባለሀብትም ባለሀብት አለ፧ የተሰኙት ርእሰ አንቀጾች በተከታታይ የወጡ እናም በጥቂት ግለሰቦች እና ድርጅቶች ላይ ያነጣጠሩ ጽሁፎች ነበሩ።

አማረ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዳሸን ቢራ ፋብሪካ ዙሪያ በወጡት ዜናዎች ምክንያት ጎንደር ድረስ ተወስዶ እንደታሰረ የሚታወቅ ነው። በወቅቱ የዳሸን ቢራ ፋብሪካን ዋና ስራ አስኪያጅ ቃለ-መጠይቅ ሲያቀርብ የነበረው የሳምሶን ማሞ «ኢትዮ-ቻነል» ነበር (አስፈላጊ ከሆነ በኢትዮ ቻነል ዙሪያ በሚቀጥለው እመለስበታለሁ)። ቃለ-መጠይቁ ረጅም እና የፋብሪካውን ስራ አስኪያጅ ሃሳብ ብቻ ያንጸባረቀ ከመሆኑ ባሻገር የሪፖርተሩን አማረ ሳይጠይቅ ያለፈ ነበር።

ከኢህአዴግ ድርጅታዊ ጉባኤ ጀምሮ በሀዋሳ በአላሙዲ «ኤልፎራ» ድርጅት ታጥሮ የተቀመጠውን እና ልማት ላይ ያልዋለውን መሬት እንዲሁም በመላ ሀገሪቱ በሁሉም ክልል ለሚድሮክ ተሰጥተው ግን ያልለሙ መሬቶችን በመጥቀስ ሚድሮክን የሚተች ተከታታይ ጽጉፍ በ«ክቡር ሚኒስትር» እንዲሁም በዜና ነክ ጽሁፎች መውጣት ጀምረው ነበር። በተለይ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ሚድሮክ በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር የማሽነሪዎች እና የእቃ ግዢ እዳ እንዳለበት ፧ በአዲስ አበባ ተሰጥቶት የነበረውን የመንገድ ፕሮጀክት እንደተነጠቀ ፧ እንዲሁም ለሲሚንቶ ፋብሪካ ተብሎ የመጡት ማሽነሪዎች ለ9 ወራት ያህል ጅቡቲ ላይ እየዛጉ እንደሆኑ እና ወደ 16 ሚሊዮን ብር ኪሳራ እንዳደረሱ ከጻፈ በኋላ ገ/ጻድቅ ህሉፍ በተባለ ጸሀፊ ማስጠንቀቂያ አዘል ተከታታይ ጽሁፎች በ«ኢትዮ-ቻነል» ጋዜጣ መውጣት ጀምረው ነበር።

ጽሁፎቹ መነሻቸውን እና መድረሻቸውን እንዲሁም በአማረ ላይ የደረሰውን አደጋ በማመዛዘን ግንኙነት እንዳላቸው እና እንደሌላቸው መተንተን ይቻላል።

አማረ አረጋዊ የኢህአዴግ ደጋፊ እንደሆነ ብዙዎች የሚናገሩለት ቢሆንም፧ የተለያዩ ጠቃሚ እና ሌሎች ጋዜጦች የማይገኙ መረጃዎችን ባሉት ምንጮች በመጠቀም በማግኘ ት ለህዝብ ይፋ የሚያደርግ ነው። ከዚህ አንጻር የአማረ እና የሪፖርተር መኖር ከጉዳቱ ጥቅሙ ያመዝናል።

ይቀጥላል።

http://www.ethiopiafirst.com/news2008/Oct/Reporter_Heluf.pdf

http://www.ethiopiafirst.com/news2008/Oct/Reporter_Heluf3.pdf

http://www.ethiopiafirst.com/news2008/Oct/YeReporter_Neger.pdf

ተጨማሪ ምንጮች

http://www.ethiopianreporter.com/content/category/14/29/1/

http://www.ethiopianreporter.com/content/category/7/36/1/